የጎንደር ሕብረት ለኢትዮጵያ አንድነት።

gonderhibrert72@gmail.com /website: www.gonderhibret.org

## ወራሪ ወያኔን ያርበደበደውን ሕዝባዊ ማዕበል ስናስብ !

**ይድረስ ለመላዉ ኢትዮጵያ ሕዝብ** ፤

**ይድረስ ለጎንደር ሕዝብ ቁጥር#11**

የጎንደር ሕብረት ለኢትዮጵያ አንድነት ተመስርቶ ከጎንደር ህዝብ ጎን ከቆመ ጀምሮ ዘርፈ ብዙ የሆነዉን በወያኔ የተጫነዉን የግፍ አገዛዝ ቀንበር አሽቀንጥሮ ለመጣል ለሚካሄደዉ ትግል በቁርጥ አጋርነት እስከመጨረሻዉ የድል ቀን አብሮ ለመጋፈጥ ቃል የገባ ድርጅት ነዉ። ለወገናችን የገባዉ ቃልም የኢትዮጵያን ልዕልና እና የህዝቦቿን ፍጹም እኩልነት የሚያስከብር ጭራሽ የማይታጠፍ ለትዉልድ የሚዘልቅ ዘመን የማይሽረዉ ቃል ነዉ።

የዚህ ጽሁፍ መልዕክት የሚያተኩረው የዛሬ አንድ ዓመት በኮሎኔል ደመቀ አኩሪ ጀግንነት ጎንደር ላይ ተቀጣጥሎ በባህር ዳር፤ ደብረ ማርቆስ፥ ናዝሬት፥ በአብዛኛው የኢትዮጵያ ክፍል የወያኔን ዘረኛ አገዛዝ ያንቀጠቀጠውን ታሪክ የማይረሳ ሕዝባዊ ተጋድሎ አንደኛ ዓመት ስናስብ በአጠቃላይ በአገራችን በኢትዮጵያ እስከአሁኗ ሰዓት እየተዋደቀ ያለውን ጀግና ትውልድ ሁሉ ታሳቢ ያደረገ እና የትግሉን አድማስ ማዶ የሚያሻግር፤ ለትብብር የሚጠራ ድርጅታዊ የትግል ጥሪ ለማስተላለፍ ጭምር ነው።

የትግራይ ነጻ አዉጭ ግንባር ዘረኛ ቡድን ለዘመናት ያህል በጎንደር ለም መሬት ላይ ዘምቶ፤ የወልቃይት ጠገዴ፤ ቃብትያ ሁመራ እና ጠለምትን ህዝብ ጨፍጭፎ ከዘር ጥፋት የተረፋትን ማንንነት ነጥቆ/ቀይሮ ለመግዛት ብዙ የጥፋት ተግባር ፈጽሟል። በቋንቋ ከመከለል ጀምሮ ለሱዳን መሬትን አሳልፎ በመስጠት እና ጎንደርን በነገድ ለመከፋፈል ያልቆፈረዉ ጉድጓድ ያልሸረበዉ የፖለቲካ ሴራ የለም።

አሻፈረኝ ብሎ የተነሳን 100-ሚሊዮን-ህዝብ አስገድዶ መምራት ከቶዉን አይችልም። የጎንደር ሕዝብ የወያኔን እብሪት ለመዋጋት በቆራጥነት ተነስቷል። መላዉ የኢትዮጵያ ህዝብም እንዲሁ በቃኝ ብሎ አዉጇል፤ በወያኔ ወታደራዊ አዋጅ በፍርሃት አይገዛም። በሃምሌ ወር አመት በሞላዉና ታሪካዊ በሆነው በጎንደር ከተማ ተለኩሶ በመላው ኢትዮጵያ ተቀጣጥሎ ወያኔ በውሸት ታሪክ የቤጌምድርን የመሬት ዘረፋ ምኞት፤ የጎንደር (ወልቃይት ጠገዴ ሕዝባችን) ዘር የማጥፋት ዕኩይ ተግባር በገሐድ ተቃውሞ የወያኔን ከንቱ ምኞት አደፍርሶታል። ሐምሌ 5 ቀን 2008 ዓ/ም ጎንደር ከተማ ላይ የነመይሳው የጀግንነት ወኔ፤ የነ ፋሲል ወርቃማ ታሪክ እንደገና የተዘመረበትና የወያኔ ቅስም የተሰበረበት ታሪካዊ ቀን ነው።

ይህ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሃያልንት ያንጸባረቀ፤ ጨለማዉን የቀደደ፤የነጻነት ትግል ብርሃን የፈነጠቀ ቀን በወርሃ ሃምሌ የአመጹ ዓመታዊ ቀን በክብር በመላዉ ዓለም ታስቦ ይዉላል። በእርግጥም በያመቱ ሊታሰብ ይገባዋል።ታላቁ የጎንደር ሰላማዊ ሰልፍ በኢትዮጵያን ህዝብ ስነ ልቦና በዕዉነት ያስተሰረየ ነዉ።

የትግራይ ነጻ አዉጭ ግንባርን አቅመ ደካማነትና ሕዝባዊ ጠላትነት ያስመሰከረ በነ ኮሎኔል ደመቀ የጀግንነት ጎራ ወያኔ የሞት ሸማ የተላበሰበት፤ አምባሻ ባንዲራ ተወርዉሮ የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማ በማዉለብለብ የኢትዮጵያን አንድነት ጥሪ የተላለፈበት አኩሪ ቀን ነበር። የጎንደር ታሪካዊ ሰልፍ በግፍ ተጨፍጭፈዉ የሞቱትን የየኦሮሞ ወጣቶችን ንጹህ ደም መፍሰስ በተባበረ ድምጽ ያወገዘ፤ የኦሮሞ ደም ደማችነዉ ብሎ ለአለም ያስተላለፈ፤ አለምን ያስደመመ፤ ወያኔን ያሸበረ ሕዝባዊ መዓበል ነበር። አሁንም ቀጥሏል።፤ ከልብ ሊታሰብ ይገባል። ወያኔ የሸበበዉን የዘር አጥር በፍቅር አንደበት ሰብሮ ለኦሮሞ ወንድሙ/እህቱ የጮኸዉ የቆራጥ ታጋይ ኢትዮጵያዊያን ታሪካዊ የአንድነት ጥሪ ቀን በእዉነትም ሊታሰብ ይገባዋል።

ይህን በጎንደር ተለኩሶ በመላው አገሪቱ የተቀጣጠለውን ታሪካዊ ቀን አክብረን ስንዉል ወያኔን አሽቀንጥሮ የመጣል ትግሉ አይቀሬ መሆኑን ለማረጋገጥ ነዉ። እኒያ የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ እያዉለበለቡ የፍትህ ታጋዩን በቀለ ገርባን መሪያችን ነዉ ፤ የፈሰሰዉን የኦሮሞ ንጹህ ደም በመዘከር ድምጻቸዉን ያሰሙ የጎንደር ፤ የባህርዳር ታጋዮች አብዛኛወቹ በወያኔ የጨለማ እስር

ቤት አካላቸዉን አተዉ የተረፋት የትግራይ ነጻዉጭ ግንባርን በመተናነቅ ላይ ያሉትን የትግል አጋርነታችን በማሳየት የጎንደርን ታሪካዊ ሰልፍ እናስባለን።

የትግል እንቁ ትዉልድ ስናስብ አማራና ቅማት በሚል ለመከፋፈል በጎንደር ላይ የሸረበዉን ሴራ ለማክሸፍ ደማቸዉ የፈሰሰዉን ወገኖቻችን በወገራ እንቃሽ፤ አምባ ጊዮርጊስ፤ ወልቃይት ጠገዴ፤ በሊቦ አዉራጅ በለሳ፤እብናት፤ አርባያ ፤ በድብረታቦ ፋርጣ ላይ፤ በጋይንት ንፋስ መዉጫ ከተማ፤ በአርማጭሆ ፤ በማዉራ ፤ በጭልጋ፤ ቋራ፤ መተማ ከወያኔ ቅጥረኞች ጋር ተናንቀዉ የተሰዉትን /የተሰቃዩትን ወንድሞች /እህቶቻችን በክብር እናስባለን።

በሱዳን ድንበር በወያኔና በሱዳን ወታደር ጥቃት ህይወታቸዉን ያጡትን እነ ጎዳናዉ አምዴን፤ የጎንደር መሬት ከተከዜ ምላሽ ነዉ በሚል አቋም ጸንተዉ እስከ እለት ሞታቸዉ የታገሉትን  እነ ታጋይ አርበኛ ጎቤን፤ አርበኛ አበራ ጎባዉ፤ አርበኛ የሻለቃ መስፍንን፤ ፤ አርበኛ ሞላ አጃዉን፤ አርበኛ ዘመነን፤ አርበኛ ያሬድን  በተጋድሎ አድናቆ እናስባለን።

ይህን ታሪካዊ ቀን ስናከብር በትግራይ ነጻ አዉጭ ግንባር የወልቃይት ጠገዴን ፤ የቃብትያ ሁመራን፤ የጠለምትን ወንድሞቻችን የዘር ጥፋት እልቂት እጅግ እያመመን ነዉ። የአማራን ዘር በመግደል በማፈናቀል በእስር በማሰቃየት ለአለፋት አርባ ዓመታት ወያኔ ትግል ከጀመረበት ሰዓት ጀምሮ አማራን ማጥፋት በሚል ፕሮግራም ያለቀዉን 5 ሚሊዮን የአማራ ህዝብን የጠፋ ህይዎት በቁጭት/በምር ሃዘን እናስባለን።

መንግስት አተዉ በሱዳን ተወስደዉ የተገደሉትን፤ መዳረሻቸዉ ጠፍቶ የቀሩትን የጋምቤላ ወንድምና እህቶቻችን፤ ሞታችሁ ሞታችን ነዉ ብለን እናስባለን። በታህሳስ 13 የተጨፈጨፉትን 400 አኝዋክ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ በሃዘን እናስባለን። በየ ክፍለጦሩ አማራና ኦሮሞ በሚል ታስረዉ የሚሰቃዩትን መኮንኖችና ወታደሮች እናስባለን

ወያኔ እርስ በርስ በማጋጨት በመሬት ነጠቃ ዘረፋ በግፍ የተገደሉትን የአምቦን፤ የናዝሬትን የሃረርን፤ የአሰላን፤የጅማን፤ የመቱን፤ የለቀምትን፤ የራያን፤ የደሴን፤ የሲዳሞን ፤ የኡጋዴንን ፤የአፋርን በተጋድሎ ወኔ እናስባለን። በኢርቻ ባል ላይ በወያኔ የዘር ማትጥፋት ዘመቻ ህይወታቸዉ ያለፈ ወንድም/ እህቶቻችን የግፍ ጭፍጨፋ  እያወገዝን የጎንደርን ታሪካዊ የአንድነት አመጽ ሰልፍ እናስባለን።

ያን ታሪክ የሰራ የጎንደር፤ የባህርዳር ትዉልድ አሻግረን ስንዘክር አጋዚን ጦር በጢማራዉ የደፋዉን በእስር የሚሰቃየዉን ኮኔሬል ደመቀንና ባልደረቦቹን እናስባለን። እነ እስክንድር ነጋን በብዕር በመጻፋቸዉ የታሰሩትን ጋዜጠኞች እናስባለን። አንዷለም አራጌን እና ለፍትህ ሲታገሉ የታሰሩ ጀጋና የትዉልድ ባለዕራይ ታጋዮችን እናስባለን።

ለፍትህ ተሟግተዉ ወያኔን በመጋፈጣቸዉ የታሰሩትን እነበቀለ ገርባን እናስባለን፤ የእምነት ነጻነት ይኑረን በማለታቸዉ ታስረዉ በደል የተፈጸመባቸዉን የሙስልም፤የክርስቲያን አባቶችን ስቃይ እናስባለን።

የዋልድባ መነኩሴወችን ግፍና እና በደል፤ ታሪካዊ ገዳሞችን/ገዳማትን እናስባለን።

ለብዙ ሺህ የወጣቶችን እና የእሴት ታጋይ አራያ የሆኑትን እነ ትግስት ይርጋን፤ እነ አስቴርን  ማሞን፤ እነ አግባዉ ሰጠኝ በዚህ ትዉልድ ስም እናስባቸዉ አለን።

ኢትዮጵያ አትከፋፈልም ብለዉ ብቸኛ ድምጽ ያሰሙትን እስከ አጽመ መቃብራቸዉ ድረስ በግፍ የተሳደዱትን  ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስን እናስባቸዋለን። በአድዋና በሁሉም የጠላት ወረራ ዘመን መስዋዕትነት ከፍለዉ የታሪክ ባለቤት ያደረጉንን ጀግና አርበኞች እንዘክራለን። በመጨረሻም በቅርብ የተለዩንን የለዉጥ የትዉልድ አርበኞች እነ ጀኔራል ጃካ ማኬሎን፤ ኮሬኔል አስናቀ እንግዳን ሌሎችም ስማቸዉን ያልጠራነ እንቁ እትዮጵያን እናስባለን። ወደፊትም ታሪካቸዉን አንድም ሳይቀር በወርቅ ቀለም ለመጻፍ ቃል እንገባለን።

የጎንደርን ታሪካዊ የአንድነት አመጽ ቀን ስናስብ የማይቀረዉ ለድል የሚያበቃን ትግል በሩቅም ሆነ በቅርብ ተባብረን መነሳት ትልቁ አቅማችን እንደሆነ እናሰምርበታለ። ይህነነ በማሰብም፤ ጎንደር ህብረት ለኢትዮጵያ አንድነት ከመሰል አጋር ድርጅቶች ማለትም ከጎጃም አለማቀፍ ትብብር፤ ከወሎ ኢትዮጵያ ቅርስና ዉርስ ማህበር፤ ከመላዉ የሸዋ ህዝብ የኢትዮጵያ አንድነት ሁለገብ ማህበር ጋር ተባብረን መስራት ቅድሚያ መሰጠት ያለበት መርሃ ግብራችን መሆኑን ተማምነንበታል። ኢትዮጵያን ከወያኔ የዘር ሥርዓት አረንቋ ለማዉጣት ክፍለ ሃገራትን ማዕከል ያደረገ የህዝብ መንግስት ማቋቋም ዋነኛ መድሃኒት ነዉ የሚለዉ የአብዛኛዉ ህዝብ ድምጽ መሆኑንም  እምነናል።

በጎህ ዕይታ በዘረኛዉ አገዛዝ አገራችን ኢትዮጵያ እንደ አገር የመኖር ህልዉናዋ ከፍተኛ አደጋ ላይ ነዉ የሚል እምነት አለን። ይህንም ለማለት ያበቃዩን ብዙ ምክንያቶች ቢኖሩም የሚከተሎት ሁኔታወች ለህዝባችን የዕለት ኑሮ መናጋት ከብዙ በጥቂቱ - - -

1ኛ የትግራይ ነጻ አዉጭ ግንባር ዘርንና ቋንቋን መሰረት ያደረገ አገዛዝ መስርቶ አንዱን ጎሳ ከሌላዉ ጎሳ የማጋጨት ፖሊሲን በማስቀጠል ማቆሚያ የሌለዉ መሆኑ

2ኛ የአንጡራ ሃብት ዘራፊ፤ የመሬት እና የማንነት ነጣቂ በመሆኑ

3ኛ የዜግነት መብት ጭራሹን በመጥፋቱ፤ ኢትዮጵያዊያን በዘራቸዉ ምልክት እየተለጠፈ ለዘላለሙ ለማጥፋት ወያኔ መርሃ ግብር በመያዙ በተለይ አማራና ኦሮሞን እርስ በእርስ ለማጫረሥ በዕርዮተ ዓለም ደረጃ ማራመዱ እና የአንድ ዘር የበላይነት መቀጠል አለበት ብሎ ማመኑና ያለማቋረጥ መተግበሩ

4ኛ የኢትዮትያን ሉዓላዊነት በመናድ ከአጎራባች አገሮች ጋር ቅንጅት ፈጥሮ መሬታችን ለሱዳን አሳልፎ በመስጠቱ እና ኢትዮጵያዊያን በሱዳን ወታደር እንዲገደሉ እንዲታሰሩ፤ ንብረታቸዉ እንዲነጠቅ በመፍቀዱ፤

5ኛ በሚስጥር የትግራይን ግፍለ ሃገር በሃገር ደረጃ ከሱዳን ጋር ስምምነቶችን በመፈረሙ አገራችን ኢትዮጵያ በማፍረስ ተግባር ላይ 50 - ድፍን - አመታት በመሰማራቱ።

6ኛ ኢትዮጵያንና ዜጎቿን በጠላትነት በመፈረጁ

የወያኔ አሰቃቂ ድርጊት አደገኝነቱ ከዓመታት ወደ ዓመታት እየባሰ የመምጣት ተጨባጭ ሁኔታወችን ስንገመግም ሃይላችን ማስተባበር ወሳኝ ተገንዝበናል። በመሆኑም ከዘር ቁራኛ ወተን ፤ ከድርጅ ፍቅር ተላቀን፤ በጾና ትብብር ለመታገል የሚያስችል አቅም መፍጠር አለብን ብለን አምነናል። ለዚህም የኢትዮጵያዉያን ሕብረት ማይከል በአስቸኳ መመስረት ቅድሚ መሰጠት ያለበት ቀዳሚ ተግባር መሂን አለበት። የዚህ ማዕከለ መሪ ዓላማወች እንደሚከተሊት ቢሆን የጎንደር ህብረት ከብዙወች ኢትዮጵያዊያን ጋር የሚጋራዉ አላማ ነዉ የሚል ከፍ ያለ ግንዛቤ አለን። አብሮ ለመስራት የሚያስችሉ - ሁኔታወች - -

1. በሕግ የበላይነት የሚያምን ተቋም /ድርጅት
2. በቋንቋ፤ በባህል ልዩ የሆኑ የተለያዩ ከ82 በላይ ነገዱች በኢትዮጵ እንዳሉ እና እኩል ዜጋ መሆናቸዉን የሚያምን
3. በአለማቀፋዊ የሰው ልጆች መብት መስፈርት የሚያምንንና የሚያስከብር
4. ቡድኖችና ግለሰቦች እንዲሁም የተለያዩ የማኅበረሰብ ስብስቦች የመሰብሰብ ፥የመደራጀት፥ ሃሳባቸውን ያለተጽኖ የመግለጽና የመጻፍ መበታቸውን የሚደገፍ
5. ግለሰቦች ወይንም ማህበረሰብ ያለምንም ጫና እና ጣልቃ ገብነት ሐይማኖታቸውን ባህላቸዉን ፤ ጥሩ ልማዳቸቸው ቢከተሉና ቢያከበሩ የማይቃወም
6. ከ 1991 ዓ ፣ም በፊት የነበረውን በአለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቀውን የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጠረፍ /ዳር ድንበር አዉቆ ይህን ለማስከበር በሚደረገዉ ማንኛውንም ዓይነት ትግል ሙሉ በሙሉ የሚደገፍ
7. ከ 1991ዓ ፣ም በፊት የነበረውን በኢትዮጵያ ውስጥ በብዙ ዘመናት ታሪክ በካርታዎች የሰፈሩትና መላው ኢትዮጵያዉያን የሚያምኑበትን በክፍለ ሐገራት መካከል ያለዉን ዳር ድንበር መመለስ የሚያምንና ለዚህም ጥረት ሙሉ ድጋፍ የሚሰጥ
8. በጎሳና በቋንቋ መከፋፈልና በነዚህ መስፈርቶች የቀበሌ የወረዳና የአዉራጃ ዘርና ቋንቋን መሰረት ያደረገን የመሬት ሽንሽናና የአስተዳደር አወቃቀርን የሚቃወም
9. በሰው ኃይል ፣በገንዘብ ፥በመረጃ ፥በዲፕሎማሲ፥ በቴክኖሎጂ እንዲሁም በተለያዩ መንገዶች በአገራችን ያለውን የአምባገነን አገዛዝ ለማስወገድ በሚደረገዉ ትግል ያለማመንታት ድጋፍ የሚሰጥ
10. ከትዉልድና ኑሮ ከመሰረቱበት የተፈናቀሉ ጎሳወች/ነገዶች ወደነበሩበት በመመለሳቸው የሚያምንና መልሶ ማቋቋምን የሚደግፍ
11. መሬታቸዉ ለውጭ ዜጋ የተሰጠባቸውን በህግና በዲፕሎማሳዊ ሂደት ተከታትሎ በማስመለስ ቁርጥ አቋም ባለዉ ፖሊሲ የሚያምን፤ ለዚህ ጥረት ደጋፊ የሆነ
12. ልዩነቶቸን በሰላማዊ ፤ ሚዛናዊ በሆነ መንገድ፤ ባልደፈረስ አካሄድ በውይይት በመፍታት የሚያምን
13. ሁሉም ኢትዮጵያዉያን በሰላም በፍቅር በመከባበር በኢትዮጵያክ ክፍለ ሃገራት አዉራጃዎችና ወረዳወች ያለምንም ገደብ እየተዘዋወሩ መስራትም ሆነ የመኖር መብታቸዉን የሚያከብርና የሚያስከብር

14. በመጨረሻም ጎሕ የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝብ የጋራ ታሪክና ባህል ያስተሳሰራቸዉ  የአንድነት ሃረግ በማጠናከር በሰላምና በፍቅር  መኖር አስፈላጊና የማይቀር ነዉ ብሎ ያምናል። ስለሆነም የህዝብ ለህዝብ ትብብርና ምክክር ይቀጥል። የጎንደር ህብረትም የድርሻዉን አስተዋጽዖ ያደርጋል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ

የትግራይ ነጻ አዉጭ ግንባር የጎንደርን ህዝብ በአየርና በመሬት ዘምቶ የመጨረሻ የዘር ማጥፋት ዝግጅቱን አጠናቋል። የአሁኑ ዘመቻ ልዩ የሚያደርገዉ ደግሞ መለዮ ለባሽ ሰራዊት ህዝባችን አንወጋም ብሎ አብዛኛዉ  ህዝባዊነቱን በማሳየቱ የትግራይ ተወላጆችን በመቶ ሽህ በማሰልጠን ከሱዳን ሁለት ክፍለጦር ተበድሮ ለማጥቃት መወሰኑ ነዉ።

በወታደራዊ አዋጅ ስም ያለዉን የሃይል ምንጭ ሁሉ ጎንደር ላይ አፍሶ የጎንደርን ህዝብ አቋም ሊያስቀይር ባለመቻሉና በማርሻል ህግ መቀጠሉን ስለመረጠ አዲስ የትጋራይ አልሞ ተኳሽ አጋዚወችን ከሱዳን ጋር ተባብሮ በኢትዮጵያ ላይ እያዘመተ ነዉ። የጎንደር ህዝብ እርሻ እንዳያርስ የሚያግድ አዋጅም አስተላልፏል። ይህን ኢሰባዊ የሆነ ዲርጊት መላዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ የታሪክ ዋልታና ማገር የሆነዉን የጎንደርን ህዝብ ያለማቋረጥ በወያኔ ጥቃት እደረሰበትን ያለዉን ወገኑን ለማዳን በአጋርነት መቆም አለበት።

ሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብ እንደሚያዉቀዉ ወያኔ ጎንደርን አጥፍቶ  ኢትዮጵያን ለማፈራረስ ቆርጦ የተነሳ ጠላት ነዉ። ይህን የጥፋት ቡድን ለአንዴና ለመጨረሻ ከበትረ ስልጣን ለማስወገድ የኢትዮጵያ ህዝብ ከዳር እስከዳር በቃን ብሎ ተባብሮ መነሳት አለበት። ወያኔ ያመጣዉን የዘር ጥቁር ሽባብ መጋረጃ ቀደን በየ ክፍለ ሃገሩ ከአዉራጃወች እስከ ትናንሽ ወረዳ/ቀበሌወች በደጋ፤ ወይና ደጋ  በቆላዉ በጠረፉ የሚኖር ሁሉ በአንድነት ቁመን ቅድስት አገራችን ኢትዮጵያን ከጥፋት መታደግ አለብን።

የጎንደር ህዝብ ከወያኔ ጋር የሚያደርገዉን ትንቅንቅ አብረን ካልቆምነ የምንወዳት አገራችን በወያኔ የጥፋት ዘመቻ የማጣት አጋጣሚ የተከሰተ መሆኑ ማሳሰብ እንፈልጋለን

በዚህ የመጨረሻዉ የነጻነት ትግል ወቅት አርሶ አደሩ፤ ተማሪ አስተማሪዉ፤መለዮ ለባሹ፤ ነጋዴዉ፤ የሃማኖት መሪወች መላዉ ህዝብ ትንሻ ትልቅ ሃብታም ድሃ ሳይል አንድ ሁኖ ይህን በዘር ተደራጅቶ የህዝብ ክብር የገፈፈዉን የትግራይ ነጻ አዉጭ ግናባርን ለማስወገድ ለግጥሚያ  በቁርጥ መቆም እጅግ አስፈላጊ እና ወቅቱ የሚጠይቀዉ አገራዊ ግዴታ ነዉ። በወያኔ አጥፊ የዘርና ቋንቋ ዕርዕዮተ ዓለም የተቋጠሩ ግለሰቦችም ሆነ ድርጅቶች ሳይዉሉ ሳያድሩ ዘረኝነትን አዉግዘዉ በአንድነት እንድንቆም ጥሪያችን እናቀርባለን። የክፍለ ሃገራት እህት ህብረቶችም  የትግሉን ማዕበል ግቡን እንዲመታ አቅጣጫ ለማስያዝ ትግሉን ለማቀናበር ተነስተዋል፤ የኢትዮጵያዉያን ህብረት ማዕከል እርሾ ለመሆን በጽኑ ዕምነት እየሰሩ ነዉ።

በመጨረሻም የነጻነት ትግሉን ለማጨናገፍ የኔ ድርጅት ይበልጣል/ይታወቅልኝ  የሚለዉ አገር በሌለበት የሥልጣን ስግብግብነት በጎበዝ አለቆች እራሥን የመከላከል በሚያደርጉት አልሞት ባይ ተጋድሎ ጀርባ ጥይት በተተኮሰ ቁጥር የኔ ድርጅት ነዉ ብሎ መፎከርን  አቁመን ከህዝባዊ ትግሉ ጎን ለመቆም እኔ ከማለት ይልቅ እኛ ብለን ታሪካዊ ትግሉ ህዝባዊ ታማኝነት አግኝቶ እንዲፋፋም በአብሮነት አርማችን አንግበን የድል ሸማ እንድንላበስ ከልብ የመነጨ ጥሪ እናስተላልፋለን።

የጎንደር ሕብረት ለኢትዮጵያ አንድነት

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ! ! !